# የኢንቨስትመንት ባንክ፡ የህግ ማዕቀፍ፣ እድሎች እና የቁጥጥር ሥርዓት

## 1. መግቢያ

ኢትዮጵያ በኢኮኖሚ ታሪኳ ወሳኝ ወቅት ላይ ትገኛለች። የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ (ESX) ወደ ሥራ መግባቱ እና የካፒታል ገበያው አዋጅ ቁጥር 1248/2021 ሙሉ በሙሉ መተግበሩ የተደራጀ የካፒታል ገበያ ጅምር ነው። ይህ የለውጥ ሥራ የተራቀቁ የፋይናንስ ሥርዓት አሳላጮች በተለይም የኢንቨስትመንት ባንኮችን አስገዳጅ ፍላጎት ይፈጥራል። የኢንቨስትመንት ባንኮች በዋነኛነት በተቀማጭ ገንዘብ ከሚቀበሉ እና ብድር መስጠት ስራ ላይ ከሚሳተፉ የንግድ ባንኮች በተለየ የካፒታል ገበያ አርክቴክቶች ሲሆኑ ለኩባንያዎች፣ መንግስታት እና ሌሎች አካላት ካፒታል ለመሰብሰብ፣ ለማሳደግ፣ ለሚዋዱ ኩባንያዎች፣ በባለስልጣኑ ቁጥጥር በሚያበቃ የኩባንያዎች ድርሻ ግዥ እና ለሌሎች ውስብስብ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግብይቶች ስልታዊ የምክር አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው።

ይህ ጽሁፍ በኢትዮጵያ ታዳጊ የካፒታል ገበያ ውስጥ የኢንቨስትመንት ባንክ እንቅስቃሴዎችን የሚመራውን የህግ እና የቁጥጥር ማዕቀፍ በተመለከተ ማብራሪያስ ይሰጣል።

***"በአዋጁ እንደተመለከተው የኢንቨስትመንት ባንክ ማለት ተቀማጭ ገንዘብ የማይሰበስብ የገንዘብ ተቋም ሆኖ የሚሸጡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን በውክልና በመሸጥ ወይም ሰነደ ሙዓለ ንዋይ አውጪውን ከገዢ ሕብረተሰብ ጋር በማገናኘት ለደንበኞቹ እንደ ደላላ እና ገንዘብ ነክ በሆኑ ጉዳዮች የአማካሪነት አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ነው።"***

አሁን ባለው የሕግ ማዕቀፍ ውስጥ የሚፈቀዱትን የተግባራት ወሰን፣ የፈቃድ መስፈርቶችን፣ ሊኖሩ የሚችሉ የገበያ እድሎችን እና ሊዳሰሱ ስለሚገባቸው ጉልህ የቁጥጥር ስነ ምህዳሮች ይዳስሳል። ገበያው ሥራውን ሲያስፋፋ የኢንቨስትመንት ባንኮች ሚና የገበያ ስፋት እና ጥልቀት (market depth) ለመገንባት፣ ቀልጣፋ የካፒታል ድልድልን ለማረጋገጥ እና የኢንቨስተሮችን እምነት ለማጎልበት ትልቅ አስተዋፅኦ ይኖረዋል።

## 2. ኢንቨስትመንት ባንክ እና የካፒታል ገበያ ህግጋት

የካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር 1248/2021 የኢንቨስትመንት ባንክን ጨምሮ ለሁሉም የካፒታል ገበያ ተዋንያን ሕጋዊ መሠረት የሚጥል ነው። ይህ አዋጅ የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣንን ዋና ተቆጣጣሪ አድርጎ የሚያቋቁም ሲሆን የሁሉም የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች የፍቃድ አሰጣጥ እና የቁጥጥር የህግ ማዕቀፎችን ይዘረዝራል።

በአዋጁ እንደተመለከተው የኢንቨስትመንት ባንክ ማለት ተቀማጭ ገንዘብ የማይሰበስብ የገንዘብ ተቋም ሆኖ በሌሎች ኩባንያዎች፣ በመንግስት ወይም በሌላ ተቋም የሚሸጡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን በውክልና

በመሸጥ ወይም ሰነደ ሙዓለ ንዋይ አውጪውን ከገዢ ሕብረተሰብ ጋር በማገናኘት ካፒታል በማሰባሰብ፣ የኩባንያዎችን ውህደት እና ዳግም መልሶ የማዋቀር ስራዎችን በማገዝ፣ ደንበኞቹ እንደ ደላላ እና ገንዘብ ነክ በሆኑ ጉዳዮች የአማካሪነት አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ነው። የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪነት ፈቃድ አሰጣጥ እና ቁጥጥር መመርያ በወሳኝ መልኩ "ኢንቨስትመንት ባንክ" በሚል የተለየ የፈቃድ ምድብ ፈጥሯል። መመሪያው በተለይ ሲጣመሩ የአንድ ኢንቨስትመንት ባንክ ዋና ተግባራት የሆኑትን በርካታ የፈቃድ መደቦችን ያመላክታል። በዚህ መሰረት የኢንቨስትመንት ባንክ ፈቃድ ያለው ድርጅት ሲሆን ያለተጨማሪ ፈቃድ የሚከተሉትን ተዛማጅ መደቦች አገልግሎት ጨምሮ መስጠት ይችላል፡፣

- የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ አከናዋኝ፡- ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለራሱ ወይም ለሌሎች ሰዎች እንደ ወኪል በመሆን የመግዛት ወይም የመሸጥ አገልግሎት፣
- የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ደላላ፡- እንደ ወኪል በመሆን የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ግዥ ወይም ሽያጭ ትዕዛዞችን የማስፈጸም አገልግሎት፣
- የኢንቨስትመንት አማካሪ፡ በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ላይ ኢንቨስት ለማድረግ ለሚፈልጉ ሰዎች ሙያዊ ምክር የሚሰጥ እና ከጉዳዩ የተገናኙ ሰነዶችን የማዘጋጀት አገልግሎት።

ከዚህ በተጨማሪ ኢንቨስትመንት ባንኮች የውክልና ሻጪነት ሚና ያላቸው ሲሆን በተለይ በመጀመሪያ ደረጃ ገበያ ላይ ከአውጪዎች ሰነዶችን በመግዛትም ሊሆን ይችላል ለሰነደ ሙዓለ ንዋይ በመሸጥ ለገዥዎች የማከፋፈል እና የመደልደል ሥራ ይሰራሉ። በሁለተኛ ደረጃ ገበያ ደግሞ ኢንቨስትመንት ባንኮች ከተቋማዊ ባለሀብቶች(Institutional Investors) የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን በመበደር፣ ለገበያ በማቅረብ በመሸጥ እና በዝቅተኛ ዋጋ መልሶ በመግዛት የገበያ ማረጋጋት እና ትክክለኛ ዋጋ ግኝት ሥርዓት ላይ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ።

እንደ ሙሉ አገልግሎት የኢንቨስትመንት ባንክ ሥራ ለመስርት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ከእነዚህ ተግባራት ውስጥ ብዙዎቹን የሚሸፍን የተቀናጀ የኢንቨስትመንት ባንክ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል። ለእያንዳንዳቸው ልዩ መስፈርቶች እና ልዩ ፈቃድ የሚጠይቁ ቢሆንም እንደ ኢንቨስትመንት ባንክ ፈቃድ ደግሞ እነዚህን ተግባራት በሙሉ የያዘ በመሆኑ አራቱንም ተግባራት ለማከናወን የሚያስችል ፈቃድ ነው።

## 3. የኢንቨስትመንት ባንክ ዋና ዋና ተግባራት

በአዋጁ እና መመሪያው ወሰን ውስጥ በኢትዮጵያ ያሉ የኢንቨስትመንት ባንኮች በርካታ ወሳኝ ተግባራትን ሊያከናውኑ ይችላሉ።

### 3.1. ካፒታል የማሰባሰብ ሥራ (የመጀመሪያ ደረጃ ገበያ ተግባራት)

ይህ በጣም አስፈላጊው የኢንቨስትመንት ባንክ ተግባር ሲሆን የሚከተሉትን ያጠቃልላል።

- **በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች በመጀመሪያ ዙር የሕዝብ ሽያጭ** (IPOs)፡- አንድን ኩባንያ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ(አክሲዮን፣ ቦንድ ወይም ሌላ ሰነድ ሊሆን ይችላል) ለሽያጭ ሲያወጣ የማማከር፣ በባለሥልጣኑ ለሚደረገው ምዝገባ ሰነዶችን

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት
Ethiopian Capital Market Administrative Tribunal
ECMAT

የማዘጋጀት፣ አቅርቦቱን ማዋቀር፣ ዋጋውን በገበያው የመወሰን እና ድርጅቱ የታሰበውን ካፒታል እንደሚሰበስብ ዋስትና መስጠት፣

- **ተከታይ የህዝብ አቅርቦቶች** (Follow-on Public Offerings)፡ቀደም ሲል የተመዘገቡ ኩባንያዎች ተጨማሪ አዲስ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለሽያጭ ሲያቀርቡ ሂደቱን በመምራት ካፒታል እንዲሰበስቡ መርዳት፣
- **የእዳ ሰነድ አወጣጥ፡** የኮርፖሬት ቦንድ ወይም የመንግስት ቦንድ አቅርቦቶችን ማዋቀር እና በውክልና መሸጥ።

### 3.2. **ውህደት እና መጠቅለል** (Merger and Acquisition) **ምክር**

በኩባንያዎች ውህደት እና አንዱ ሌላውን የመግዛት፣ ድርጅቶችን መልሶ ማዋቀር አይነት ተግባራት ውስጥ ኢንቨስትመንት ባንኮች እንደ ስትራቴጂካዊ አማካሪዎች ሆነው ያገለግላሉ። እነዚህ ተግባራት የሚከተሉትን ያካትታሉ።

- ትመና፡- የአንድን ኩባንያ ትክክለኛ ዋጋ መወሰን፣
- ከመዋሃድ፣ አንድ ድርጅት የራሱ በሆነ ሌላ ድርጅት ውስጥ ያለውን ድርሻ ከመሸጥ ከመጣመር እንዲሁም ሌሎች ሰነደ ሙዓለ ንዋይ መግዛትና መሸጥ የሚጠይቁ የድርጅት ገንዘብ ማስተዳደር፣
- ድርድር ወቅት ድጋፍ ማድረግ- በድርድር እና በፋይናንስ ዝግጅት ላይ እገዛ ማድረግ፣
- ገለልተኛ አስተያየቶችን ለውሳኔ ሃሳብ ማቅረብ፡ ስለ ግብይት ዋጋ ፍትሃዊነት ገለልተኛ አስተያየቶችን ለኩባንያው የዳይሬክተሮች ቦርድ መስጠት።

### 3.3. **ግብይት (የሁለተኛ ደረጃ ገበያ ተግባራት)**

ኢንቨስትመንት ባንኮች የደንበኞችን የመሸጥ ወይም የመግዛት ትዕዛዞችን ለመፈጸም የገበያ ከፋች(market maker) ተግባራትን ያከናውናሉ። ይህም ዋንኛው አላማው ሁሌም ለሚሸጡት ሰነደ ሙዓለ ንዋይ በገበያው የመግዛት እና የመሸጥ አዝማምያ በመፍጠር (Liquidity) የሰነደ ሙዓለ ንዋዩን ተፈላጊነት ለመጨመር ነው። የኢንቨስትመንት ባንኮች በውክልና ከመሸጥ ባሻገር የተስማሙባቸውን ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች በመግዛትና በመሸጥ አንዳንዴም ተብድረው በመሸጥ በገበያው ዘላቂነት ያለው የሽያጭ እና ግዥ ሁኔታ እንዲኖር በማድረግ ለገበያው መረጋጋትን ይፈጥራሉ። ከዚህ በተጨማሪ ራሳቸውን በሁለት ወገን በማድረግ እንደ ገዥ እና ሻጭ የመግዣ እና የመሸጫ ዋጋ በማስገባት የገበያ ከፋች ሚና በመጫወት ገበያው ተገማች እና የተረጋጋ እንዲሆን ይረዳሉ።

### 3.4. **ኢንቨስትመንት ባንክ እና ምርምር**(Research)

ኢንቨስትመንት ባንኮች ከፍተኛ ጥራት ያለው ገለልተኛ የሆነ በተለይ ቋሚ ገቢ የሚያስገኙ የእዳ ሰነዶች እንዲሁም አዋጭ በሆኑ የድርሻ ሰነዶች በሚያወጡ እና በሚሸጡ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ላይ ጥናት እና ትንተና በማውጣት ለተቋማዊ እና ሌሎች ኢንቨስተሮች የኢንቨስትመንት ውሳኔዎችን የሚደግፍ ቁልፍ አገልግሎት ይሰጣሉ።

## 4. **የኢንቨስትመንት ባንክ ፈቃድ አሰጣጥ እና የቁጥጥር ማእቀፍ**

ኢትዮጵያ ውስጥ የኢንቨስትመንት ባንክ የማቋቋም ሂደት በባለሥልጣኑ ቁጥጥር የሚመራ ነው።

የኢንቨስትመንት ባንክ ለማቋቋም መሟላት ከሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

### 4.1. ጥብቅ ካፒታል መስፈርቶች

የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪነት ፈቃድ ለማግኘት ከሚያስፈልጉ ዋና መስፈርቶች አንዱ እና ዋነኛው ለዘርፉ የሚፈለገውን ካፒታል ማሟላት ነው፡ ፡ የፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ ለእያንዳንዱ የፈቃድ አይነት አነስተኛ የካፒታል መስፈርቶችን አስቀምጧል፡፡ ብዙ ፈቃዶችን አጠቃሎ አገልግሎት ለሚሰጥ ድርጅት ኃላፊነቱም ከፍተኛ በመሆኑ ለኢንቨስትመንት ባንክ የሚጠየቀው አነስተኛ የካፒታል መመዘኛ መስፈርት ከፍ ያለ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ የኢንቨስትመንት ባንክ አገልግሎት ለመስጠት ፈቃድ ለማውጣት የሚያስፈልገው አነስተኛ የካፒታል መስፈርት መደበኛ ባንክ ለሆኑት ብር 100 ሚሊዮን ሲሆን ለሌሎች ድርጅቶች ደግሞ ብር 25 ሚሊዮን ነው፡፡

### 4.2. የኢንቨስትመንት ባንክ የብቁነት እና ተገቢነት መመዘኛዎች

ባለሥልጣኑ የአንድን የኢንቨስትመንት ባንክ ዳይሬክተሮች፣ አመራሮች እና ዋና ሰራተኞች ብቃት፣ ልምድ እና ታማኝነት በጥብቅ ይገመግማል፡፡ ይህ የብቁነት እና ተገቢነት መስፈርት ግምገማ የተጠቀሱት የድርጅት ሃላፊዎችን መልካም ስም ያላቸው መሆን አለመሆኑን፣ ከዚህ በፊት በፋይናንስ እና እምነት ማጉደል ወንጀሎች ተቀጥተው የሚያውቁ መሆን አለመሆኑን፣ ከዚህ በፊት የመክሰር ውሳኔ ተላልፎባቸው ከሆነ እና ሌሎች ዝርዝር መለኪያዎችን ይይዛል፡፡ ይህ የግምገማ ሥርዓት ድርጅቱ ፈቃድ ሲጠይቅ እና ፈቃድ ተሰጥቶት በሚሰራበት ጊዜ ሁሉ የሚከናወን ተግባር ነው፡፡

## 5. ኢንቨስትመንት ባንክ በገበያ ልማት ውስጥ ያለው ወሳኝ ሚና

አቅም ያላቸው የኢንቨስትመንት ባንኮች በተሳካ ሁኔታ ወደ ገበያው መግባት የንግድ ዕድል ብቻ ሳይሆን ለጤናማ የካፒታል ገበያ ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የኢንቨስትመንት ባንኮችን ሚና በጥቂቱ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

### 5.1. የዋጋ ግኝት እና የመጀመሪያ ደረጃ ገበያ ዋጋ

በኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ለተመዘገቡ የመጀመሪያ ኩባንያዎች ቁልፍ ፈተና ትክክለኛ ዋጋ መወሰን ነው፡፡ የኢንቨስትመንት ባንኮች የዋጋ ተመን የግምገማ እውቀታቸውን እና የኢንቬስተር ኔትወርኮችን በመጠቀም ለዚህ ሂደት አስፈላጊ ጥናት በማድረግ ኩባንያዎች ዝቅተኛ ዋጋ እንዳይኖራቸው እና ኢንቨስተሮች ከልክ በላይ ክፍያ እንዳይከፍሉ ለማድረግ ትክክለኛ ዋጋ ግኝት ሂደት ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ፡፡

### 5.2. የኢንቨስተሮችን መተማመን መገንባት

መልካም ስም ባለው የኢንቨስትመንት ባንክ የተከናወነ ተገቢ ትጋት (Due Diligence) ለገበያ የጥራት ምልክት ሆኖ ያገለግላል፡፡ የኢንቨስትመንት ባንክ ተሳትፎ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አውጪው መረጃ የተጣራ መሆኑን እና የተገለጸው መረጃ አስተማማኝ ስለመሆኑ ዋስትና የሚሰጥ ነው፡፡

### 5.3. የገንዘብ ዋጋ ያላቸው ሰነዶችን መፍጠር (Product Innovation)

ገበያው እየዳበረ ሲመጣ የኢንቨስትመንት ባንኮች ገበያውን ለማስፋት እና የተለያዩ የኢንቨስተሮችን ፍላጎቶች ለማሟላት ወሳኝ የሆኑ በሀብት የተደገፉ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች(Asset Backed Securities)፣ ተዛማጅ ውሎች (Derivatives) እና ከአረንጓዴ ልማት ጋር በተያያዘ የሚወጡ የእዳ ሰነዶች(Green Bonds) ያሉ አዳዲስ የፋይናንስ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች በማዘጋጀት ግንባር ቀደም ይሆናሉ ተብሎ ይጠበቃል።

### 5.4. የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ከፊል ወደ ህዝብ ኩባንያ የመለወጥ እቅድ የማማከር አገልግሎት

የሃገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያውን ተከትሎ ኢትዮጵያ የመንግስት የልማት ድርጅቶችን በከፊል ወደ ግል የማዞር ፖሊሲ (Privatization and Liberalization) ትልቅ እድልን ይዞ ይመጣል ተብሎ ይጠበቃል። በዚህ ረገድ በትላልቅ የፕራይቬታይዜሽን ስራዎች ልምድ ያላቸው የኢንቨስትመንት ባንኮች የልማት ድርጅቶችን ዋጋ ተገቢ ትመና በማውጣት እና ውስብስብ ግብይቶች በማዋቀር ረገድ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ ተብሎ ይገመታል።

## 6. እየተሻሻለ የመጣው የተወዳዳሪ ገጽታ

አለምአቀፍ ተዋናዮች፡ አለምአቀፍ የኢንቨስትመንት ባንኮች ከሀገር ውስጥ ኢንቨስትመንት ባንኮች እና ኩባንያዎች ጋር በጥምረት ሲሰሩ ወይም የሀገር ውስጥ ቅርንጫፎችን ሊመሰርቱ፣ አለምአቀፍ እውቀትን በማምጣት በአካባቢያዊ አውድ ላይ ከፍተኛ የሆነ የእውቀት ሽግግር ሊያስከትል እንደሚችል ይጠበቃል።

የሀገር ውስጥ ቀዳሚዎች፡ የሃገር ውስጥ ጀማሪ ኢንቨስትመንት ባንኮች ለትልልቅ ድርጅቶች የምክር አገልግሎት እና በመካከለኛ ገበያ ደረጃ ያሉ ኩባንያዎችን የውህደት እና የመግዛት ሥራዎች ላይ በማተኮር አገልግሎት ሊሰጡ ይችላሉ። ንግድ ባንኮች ነባር የሆነውን የደንበኞቻቸውን ግንኙነት በመጠቀም የኢንቨስትመንት ባንክ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ መደረጉ ለዘርፉ እድገት ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። ይህ ሲሆን በንግድ ባንኮች የሚገኘው የአስቀማጮች ገንዘብ ጥበቃ የሚያስፈልገው እና ከአደጋ ነጻ መሆን ስለሚገባው ንግድ ባንኮች ሃላፊነቱ የተለየ ተቀጽላ ድርጅት በማቋቋም ከብሔራዊ ባንክ ተቃውሞ እንደሌለ ከተረጋገጠ በኋላ በባለሥልጣኑ የሚፈለገውን እና በመመሪያው የተቀመጠውን መስፈርት ሲያሟሉ የኢንቨስትመንት ባንክ ፈቃድ ሲሰጣቸው ስራውን እንዲሰሩ መፈቀዱ ተገቢ ነው።

## 7. መደምደሚያ

በኢትዮጵያ መደበኛ የካፒታል ገበያ መቋቋም ለኢንቨስትመንት ባንኮች እድገት ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር ክስተት ነው። አሁን በሥራ ላይ ባለው የካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር 1248/2021 እና የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪነት ፈቃድ አሰጣጥ እና ቁጥጥር መመሪያ ቁ.980/2016 መሠረት አመልካቾች ለኢንቨስትመንት ባንክ ፈቃድ የተቀመጡ መስፈርቶችን ሲያሟሉ ባለሥልጣኑ ፈቃድ ይሰጣቸዋል። በዚህ መሰረት ኢንቨስትመንት ባንኮቹ በቁጥጥር ማዕቀፉ ስር ሆኖ የተፈቀደላቸውን ተግባራት ብቻ በማከናወን ለገበያው እና ለኢኮኖሚው እድገት ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ ተብሎ ይጠበቃል።

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ችሎት
Ethiopian Capital Market Administrative Tribunal
ECMAT

የዚህ አዲስ የፋይናንሺያል ስነ-ምህዳር ስኬት በኢንቨስትመንት ባንኮች አቅም እና ታማኝነት ላይ የተመሰረተ ነው ማለት ይቻላል። የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዞችን ማደግ ከሚያስፈልጋቸው ካፒታል ጋር የሚያስተሳስሩ፣ በኩባንያ ሪስትራክቼሪንግ፣ ውህደት እና መጠቅለል እንዲሁም በፕራይቬታይዜሽን ግብይቶች ላይ በማማከር ኢኮኖሚውን የሚያሻሽል ወሳኝ የገበያ ተዋናይ ይሆናሉ ተብሎ ይጠበቃል። በመጨረሻም ለበለፀገ ገበያ መሠረት የሆነውን በገበያው መተማመንን ይገነባሉ ተብሎ ይገመታል። ለተቆጣጠሪዎችም ሆነ ለገበያ ተሳታፊዎች፣ መጪዎቹ ዓመታት ከፍተኛ የትምህርት፣ የመላመድ እና የትብብር ጊዜ ይሆናል። የኢንቨስትመንት ባንኮች የሚቀጥለውን የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ታሪክ ምዕራፍ ለመጻፍ ግንባር ቀደም ሚና ይጫወታሉ።